# የግብር ከፋዮች የሶስተኛ ወገን የግብርና ታክስ
# አከፋፈል ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ገባ 10/2001

## 1. መግቢያ

የግብር ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራሙ ቀጣይነት እንደኖረው እና የግብር አስተዳደሩን ዘመናዊ ከማድረግ አኳያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በግብር ህጐቹ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የግብር ዕዳውን ለመክፈል ወደ ገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ሲቀርብ ግልፅ፣ቀልጣፋና ምቹ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን አሠራር በየጊዜው እያሻሻለና ሥራ ላይ እያዋለ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ግብር ከፋዩ ከአሁኑ በፊት በገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ብቻ ቀርቦ ግብርና ታክሱን ይከፍልበት የነበረውን የአሠራር ስርዓት በማሻሻል በሶስተኛ ወገን /በፋይናንስ/ ተቋማት በኩል ቀርበው የሚከፍሉበትን ስርዓት አመቻችቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የግብር ከፋዬች የሶስተኛ ወገን የግብርና ታክስ አከፋፈል ሥርዓት ለመወሰን የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ገባ/10/2001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት

በገቢ ግብር አዋጅ 76/94 አንቀጽ 67 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ግብር ከፋዮች በገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት በኩል ብቻ እንዲከፍሉ ይደነግግ ስለነበረ አሁን በአዲስ ስራ መልክ ሲደራጅ በሶስተኛ ወገን መክፈል የሚችሉበት ሁኔታ በህጉ የተሻሻለ በመሆኑ ይህን የአሠራር ስርዓት ለመተግበር መመሪያውን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## 4. አውጭው ባለስልጣን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1998 አንቀጽ 17 ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ለማውጣት ስልጣን በተሰጠው መሠረት ለሙከራ ትግበራ ወቅት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 5. ትርጓሜ

“የሶስተኛ ወገን ገቢ አሰባሰብ” ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ላይ በተዘረዘሩት የገቢ አይነቶች ከግብር ከፋዬች የሚፈለጉ የግብርና ታክስ ዕዳዎችን ከገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ጋር ስምምነት በፈፀሙ ባንኮች ፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማት እና ፖስታ ቤት በኩል የሚደረግ የመሰብሰብ የአከፋፈል ስርዓት ነው፡፡

“የአከፋፈል ስርዓት” ማለት ግብር ከፋዮች በግብር ህጉ በሚሸፈኑ ማናቸውም ገቢዎችው ላይ በግብር ህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ቀርበው የሚፈፅሙበትን ክፍያና ገቢው ሰብሳቢ መ/ቤት ወይም እሱ በሚወክለው ሶስተኛ ወገን የገንዘብ ተቋም የሚከናወነውን የአሰባሰብ ሂደት የሚገልፅ ነው፡፡

## 6. ዓላማ

- ግብር ከፋዮች ወደ ገቢ ጽ/ቤቶች የግድ መምጣት ሳያስፈልጋቸው ያለውጣ ውረድ በአቅራቢያቸው በሚገኝ የፋይናንስ ተቋም የሚፈለግባቸውን ታክስ በወቅቱ መቀጫ ውስጥ ሳይገቡ ለመክፈል ያስችላቸዋል፡፡
- ግብር አስገቢው መ/ቤት ግብሩን ለመሰብሰብ ሲል በሚሰጠው አገልግሎት ላይ የሚፈጠረውን ጫና ይቀንሳል፡፡
- መከፈል ያለበት የግብር ታክስ ዕዳ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ይረዳል፡፡
- የግብር አከፋፈሉና አሰባሰቡ ስርዓት ለግብር ከፋዩም ሆነ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የገንዘቡን እንቅስቃሴ ደህንነት አስተማማኝ ያደርጋል፡፡

## 7. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ የሚገኙ ግብር ከፋዮች በመመሪያው አንቀጽ 10 ከቁጥር 10.1 እስከ 10.7 በተዘረዘሩት የገቢ/የግብርና ታክስ ዓይነቶች ከገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ጋር ስምምነት በፈፀሙ የገንዘብ ተቋማት ብቻ ላይ የሚከናወን አሰባሰብ ይሆናል፡፡

## 8. የሶስተኛው ወገን አከፋፈል ሥርዓት የሚከናወንበት ሁኔታ

1. ግብር ከፋዩ ከሶስተኛ ወገን ላይ በሚገኘው የገቢ ማስታወቂያ ቅጽ ገቢውን አስታውቆ መክፈል ያለበትን ግብርና ታክስ በግብር ህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መክፈል አለበት፡፡
2. ግብር ከፋዩ የሚከፍለው ግብርና ታክስ ማህደሩ በሚገኝበት ከተማ በሚገኝ የሶስተኛ ወገን የገንዘብ ተቋም መሆን አለበት፡፡
3. በሶስተኛ ወገን የሚደረግ የግብር/ታክስ የአከፋፈል ስርዓት ተግባራዊ የሚሆነው ከገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ጋር ውል የፈፀመ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡
4. ጊዜ ያለፈባቸው ውዝፍ የግብርና ታክስ ዕዳ ክፍያዎች በሶስተኛው ወገን የአከፋፈል ስርዓት የሚስተናገዱ አይሆንም፡፡

## 9. በሶስተኛ ወገን አከፋፈል ስርዓት የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 9.1 በግብር ከፋዮች

ሀ. ሶስተኛ ወገን የገንዘብ ተቋሙ የሚገኝበት ከተማ መሆኑን የሚገልጽ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ይዞ የመቅረብ፣

ለ. ገቢ ሰብሳቢው ሶስተኛ የፋይናንስ ተቋም አገልግሎቱን ለመስጠት ከገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ጋር ውል የተፈራረመ መሆኑን የማረጋገጥ፣

ሐ. የመደበኛ ቁርጥ ግብር ከፋይ ከሆነ በየዓመቱ የመደበኛ ቁርጥ ግብር እና ታክስ ተመኑን የመክፈል፣

መ. ማህደሩ በሚገኝበት ከተማ በሚገኝ የ3ኛ ወገን የገንዘብ ተቋም በግብር ዘመኑ ወይም የግብር ዘመኑ ሲያልቅ የሚታሰብ አስቀድሞ የመክፈል፣

ሠ. በ3ኛ ወገን የገንዘብ ተቋም የሚጠየቀውን የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል

ረ. የግብርና ታክስ ክፍያ ማስረጃውን በተጠየቀ ጊዜ የማቅረብ የውዝፍ ግብር ዕዳ ከሆነ የግብር/ታክስ ዕዳውን እንዲከፍል የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ሲደርሰው ብቻ ክፍያውን የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

### 9.2 በሶስተኛ ወገን ገቢ ሰብሳቢ አካላት

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ከተራ ቁጥር 10.1 እስከ 10.7 በተዘረዘሩት ውስጥ የሚሸፈኑ የገቢግብርና ታክስ ዓይነቶችን የመሰብሰብ፣

ለ ከግብር አስገቢው መ/ቤት የሚሰጡ ግብር ከፋዩ ገቢውን የሚያሳውቅባቸውን የገቢ ማስታወቂያ ቅፆች በበቂ መጠን መኖራቸውን የማረጋገጥና ግብር ከፋዩ ለክፍያ ሲመጣ የመስጠት፣

ሐ. ግብር ከፋዩ የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ያለው መሆኑንና የግብር ከፋይነት ማህደሩ ተቋሙ በሚገኝበት ከተማ የሚኖር መሆን ከመለያ ቁጥሩ ሰርተፊኬት ላይ አይቶ የማረጋገጥ፣

መ. የግብር ከፋዩን የክፍያ ማስረጃ በወቅቱ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት መላክ፣

ሠ. የተሰበሰበውን ገቢ በየዕለቱ በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የባንክ ሂሳብ ውስጥ ማስገባት፣

ረ. የዘመኑ የግብር ዕዳ ክፍያ ብቻ መሆኑን/ውዝፍ ግብር አለመሆኑን በማረጋገጥ ገቢውን የመቀበል፣

ሰ. በየክፍያው ዓይነት በተዘጋጀው ደረሰኝ የክፍያ መጠኑንና ጊዜ/የወር፣የ3ወር፣የዓመት እንደክፍያው ዓይነት አረጋግጦ የመሙላት፣

ሸ. የተጨ/እሴ/ታ ክፍያ ሲፈፀም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የተጠቀሰውን የምዝገባ ቁጥር በታክስ ማስታወቂያ ቅጽና በደረሰኙ ላይ የመሙላት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

9.3 በገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት

ሀ. በሶስተኛ ወገን የተሰበሰበን የግብር ከፋዩን የክፍያ ማስረጃ ከማህደሩ ጋር በማያያዝ የግብር ከፋዩን የግብር ታክስ ዕዳ ሚዛን ወቅታዊ አድርጎ የመያዝ፣ዕዳ ከሌለበት የንግድ ፈቃድ ዕድሳት ክሊራንስ ተዘጋጅቶ እንዲደርሰው ማድረግ ፣

ለ. ከሶስተኛ ወገን ግብር ሰብሳቢ ተቋም ጋር የውል ስምምነት መውሰድና ለግብር ከፋዮች ማሳወቅ፣

10. <u>በሶስተኛ ወገን ሰብሳቢ የገንዘብ ተቋማት የሚሸፈኑ የገቢ ዓይነቶች</u>

10.1 የደመወዝ ገቢ ግብር /1101-2/

10.2 የንግድ ትርፍ ግብር /1103/

10.3 የኪራይ ገቢ ግብር /1102/

10.4 የተርን ኦቨር ታክስ

10.5 የተጨማሪ እሴት ታክስ /1120-1190/

10.6 ከተከፋይ ሂሳብ የተቀነሰ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር /1103/

10.7 የእርሻ ስራ ገቢ ግብር/1107/

10.8 የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ/1468/

11. መመሪያው ተፈፃሚነት የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የገቢዎች ባለሥልጣን

<u>ባሕር ዳር</u>